ታላቁ ተጋድሎ

የ10ኛ ትምህርት መምሪያ

የትምህርቱ መሪ ጥቅስ፤ 1ተሰሎንቄ 4:16-17

የትምህርቱ ዋና ሐሳቦች

በታላቁ ተጋድሎ ሒደት ከሞናገኛቸው የዲያቢሎስ ማሳሳቻ መንገዶች አንዱና አሰይጣን ውጤታማነት አስተዋጽዖ ያደረገ ትምህርት መናፍስት ጠሪነት ነው። ይህ ልሞምድ ከክርስትና ውጪ አጋንንትን በመሳብና ከአጋንንት ጋር በመገናኘት የሚካሄድ ሲሆን ወደ ክርስትና ግን በዘህ መልኩ ሳይሆን መልኩን ቀይሮና የክርስትናን ካባን ለብሶ እንደገባ እናስተውላለን። በተለይ ይህ አስተምህሮ ሰው ሲሞት ነፍሱ ትወጣለች፤ ከርሱ ተለይታ ራሷን የቻለችና ጎልውና ያላት ሆና ወይ ወደ ገነት ወይሞ ወደ ሲዖል ተገባለች፤ ሰው ሲሞት ነፍሱ አትሞትም በሚል አሳሳች ትምህርት የመጽሐፍ ቅዱስን ጥቅሶች አጣሞሞ በመጥቀስ ወደ ክርስትና የገባ ነው። ትምህርቱ ከተለያዩ ቦታዎች ተቀነባብሮ የመጣ ሲሆን በተለይ ወደ ክርስትና የገባው ግን ከግሪክ ፍልስፍና ጋር ተያይዞ ነው። በግሪክ ፍልስፍና መሠረት ሰው የአካልና የነፍስ ውጤት ነው፤ አካል የረከሰ፣ የማይረባና ሟች፣ ነፍስን አንቆ የያዘ ብልሹ ነገር ነው፤ ስለዘህ ይህንን ሟች አካል የፈለጉትን እየበሉና እየጠጡ ማርከስ ያስፈልጋል፤ ነፍስ ግን ቅዱስና ውብ ነገር ነች፤ ሰው ሲሞት ይቺ ነፍስ ከሟች አካሉ ተለይታ እፎይታን ታገኛለች የሚል ነው። ይህንን ዓለማዊ አስተሳሰብ እንደነ አውጉስጢን ያሉ የክርስትና ፍልስፍና መሪዎች አጥሞቀውና የክርስትና ካባ አልብሰው ወደ ቤ/ክ አስገቡት፤ በውጤቱም የክርስቲያኑ ዓለሙ ነፍስ አትሞትም፤ ሰው ሲሞት ጥሩ ሰው ከነበረ ወደ መንግሥተ ሰማያት በደስታና ፍሰሐ፤ ካልሆነ ደግሞ ለዘላለም እየተቃጠለ በገሃነም ይኖራል የሚል እጅግ መሐሪና እጅግ አፍቃሪ የሆነው የቅዱስ እግዘአብሔርን ስሙ የሚያጎደፍ ትምህርት ወደ ክርስትና እንዲገባ ሆነ። ባለፉት ትምህርቶች የዲያቢሎስ ዋነኛ ሐሳብ የእግዘአብሔርን ስሙ ማጠልሸት እንደሆነ በተማርነው መሠረት ይህ የነፍስ አትሞትሞና መናፍስትን የመጥራት ልሞምድ በበኩሉ ክርስቲያናዊ ስሙ ተሰጥቶት፣ በተጣመሙ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ታጅቦና ዘመናዊነትን ተላብሶ የክርስትናው ዓለሙ ዋነኛ አስተምህሮ ሆኗል። ዘመነ እያለቀ ባለበት ባሁኑ ገዜና ፍጻሜ ዓለሙ ከመሆኑ በፊት መልኩን ቀይሮ ከድንቅና ተዓምራት ጋር ተቀላቅሎ ብዙዎችን የሚያስት ረቂቅ ትምህርት ሆኖ ይቀርባል። በዘህ ሳምንት ጥናታችን የሚከተሉትን 3 ነጥቦች በዋነኛነት እንማራለን፡-

1. **የመናፍስት ጠሪነት ዋናው ፍሬ ነገርና ዓላማ በተለይሞ ከታላቁ ተጋድሎ አኳያ ሰብዓዊ ዘርን ማሳሳትና ከአጋንንት ኃይሎች ጋር ማወዳጀት መሆኑን**
2. **መጽሐፍ ቅዱስ እንዲሚያስተምረው ሰው የተፈጠረው ከሞድር አፈርና ከእግዘአብሔር አስትንፋስ እንደሆነ፤ የመጀመሪያው ሞት እንቅልፍ እንደሆነ፤ ሁለተኛው ሞት ግን ትንሣኤ የሌለበት ፈጽሞ መጥፋት እንደሆነና ይህም መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው ገሃነም እሣት የሚባለውን እንደሚጠቁሞ**
   የእግዘአብሔር ቃል የሚሰጠን እውነተኛ ተስፋ ትንሣኤ ሙታን ሆኖ ሰብዓዊ ዘር ለዘላለም ከእግዘአብሔር ጋር የሚኖር መሆኑን ነው

1. የጣዖት አምልኮ ልምምድ ወደ ቤክ ሠርጎ ገባ፤

- **በማቴዎስ 10:28 ኢየሱስ ነፍስ አትሞትም ብሎ አላስተማረም**
- **ነፍሳችን የማትሞት ከሆነ ለምን ትንሣኤ አስፈለገ? (ዮሐ 6:39-40)**
- **ለዘላለም የማይሞት ማነው? (1ኛ ጢሞ 6:13-16)**
- **በኢየሱስ የተዋጁ ዘላለማዊነትን የሚቀዳጁት መቼ ነው?(1ቆሮ 15:51-55)**
- **ነፍስ አትሞትም የሚለው ትምህርት መቼና እንዴት ወደ ቤ/ክ ገባ?**
- **ነፍስ አትሞትም የሚለው አስተምህሮ ለምንድነው አደገኛ የሆነው?**

2. ሕይወትና ሞት በብሉይ ኪዳን፤

- **በዘፍጥረት 2:7 መሠረት እኛ ነፍስ ነው ወይስ ነፍስ ያለብን የምንባለው?**
- **ስንሞት ምን እንሆናለን? መዝ13:3፤17:15፤ 115:17፤146:2-4፤ መክ 9:5**
- **ዳንኤል 12:2 በሞት ስላንቀላፋት ምን ይላል? (ዮሐ 5:25-29)**

3. ሕይወትና ሞት በአዲስ ኪዳን፤

- **የዓልአዛር ከሞት ስለ መነሳት ምን ያስተምረናል? (ዮሐ 11:11-14፤ 21-25)**
- **ጳውሎስ ስለ ሞት ምንድነው ያስተማረው? ትንሣኤስ እንደዘህ ወሳኝ ስለ መሆኑን ምንድነው ያለው? (1ተሰ 4:13-17 እና 1ቆሮ 15:12-23)**
- **እናስ በአዳኛችን በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባለን እምነት ምን ተስፋ አለን? (2ጢሞ 1:10፤ 1ጴጥ 1:3-4)**

4. መናፍስት ጠሪነት በመጨረሻው ዘመን፤

- **ስለ መጨረሻው ዘመን ማሳሳቻዎች ጳውሎስ ምን አለ? (2ተሰ 2:7-9፤ 2ቆሮ 11:13-14)**
- **ሐሰተኛ አስተማሪዎች ድንቅና ምልክት በማን ኃይል ነው የሚያደርጉት? (ማቴ 7:21-23)**
- **ከጳውሎስ ሌላ የሐንስ ስለ መጨረሻው ዘመን ማሳሳቻ ምን ትንቢት ተናግሯል፤ (ራዕ 13:11-14፤ 16:13-14)**
- **ጌታችንስ ስለ መጨረሻው ዘመን ማሳሳቻ ምን አለ? (ማቴ 24:21-26)**
- **በአካባቢዎ የመናፍስት ጠሪነት ልሞምድ በምን ደረጃ ላይ ይገኛል? እየዘመነና እየረቀቀ የመጣውን አሠራር ያስተውሉታል?**
- **ከዘህ መዓት እንዴት እንጠበቅ? (መዝ 119:105፤ ኢሳ 8:19-20)**
- **ስለዘህ ከዘህ ትምህርት አንጻር "ነፍስ ይማር" ብሎ መናገርን እንዴት ይታያል?**

ቴሌግራም፡ @giziew7 | ስልክ፡ 0949-61 11 11 | 0717-96 43 73 | email: editor@giziew.org | fb.me/giziew7 | YouTube: @Giziew | https://www.giziew.org/